22070016

IBO IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2**

Wednesday 16 May 2007 (morning)
Mercredi 16 mai 2007 (matin)
Miércoles 16 de mayo de 2007 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.
- Vous n'êtes pas autorisé(e) à amener des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d'examen.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.
- No se permite traer a la sala de examen copias de las obras estudiadas.



© IBO 2007

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም::*

**ድራማ**

1. ተከታዩን

(ሀ) ከትራጀዲ ጋር ሲወዳደር ኮመዲ ቀለል ያለና ፈገግ የሚያሰኝ ቢሆንም በሚያስተላልፈው ቁምነገር ከትራጀዲ የሚያንስ አይደለም:: ኮመዲ ይህንን የሚያደርገው እንደምን እንደሆነ ያጠናሃቸውን ድራማዎች በማወዳደር አሳይ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ተውኔት በተዋንያኑ አማካኝነት ድርጊትን የሚያቀርብ በመሆኑ በተመልካቹ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀጥተኛ ነው:: የተዋንያኑ ችሎታም የተጽእኖውን መጠን ይወስነዋል:: ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ደራስያኑ ተዋንያኑን በድርጊት ለማቅረብ የሞከሩበትን መንገድ አብራራ::

**ረጅም ልቦለድ**

2. ተከታዩን

(ሀ) የልቦለድ ታሪክ ትኩስና የሚስብ መሆን አለበት:: ታሪኩን ታሪክ የሚያሰኘው በውስጡ የለውጥ ሂደትን በማቅረቡ ነው:: ይህንን ሃሳብ ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር አስረዳ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) የረጅም ልቦለድ አንባቢ ገፀባህሪውን እንዲረዳ ደራሲው ገፀባህሪውን በድርጊት ማሳየት መቻል አለበት:: ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ የደራስያኑን የአቀራረብ ችሎታ አብራራ::

**ስነግጥም**

3. ተከታዩን

(ሀ) የግጥም ዋነኛ ትኩረት የሰው ልጆች የህይወት ገጠመኝ ነው፡፡ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሶስት ግጥሞች በመመርኮዝ ግለጽ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) ስነግጥም የተሰራው በቃላት በመሆኑ የቃላት ምርጫ በስነግጥም ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ በዚህ ሃሳብ ምን ያህል ትስማማለህ? መልስህ ቢያንስ ያጠናሃቸውን ሶስት ስራዎች በምሳሌነት የሚያወዳድር ይሁን፡፡

**ዝርው (ከረጅምና አጭር ልቦለድ ሌላ)**

4. ተከታዩን

(ሀ) የአንድ ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) መግቢያ የአንባቢውን ትኩረት የሚስብና ተከታዩን የጽሁፍ ክፍል የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ ትክክለኛ መሆኑን ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማወዳደር አስረዳ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) አንባቢው ስራውን አንብቦ የሚረዳበትን የተለየ መንገድ ማመላከት አለበት፡፡ ያነበብካቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ሃሳቡን አስረዳ፡፡

**አጭር ልቦለድ**

5. ተከታዩን

(ሀ) በአጭር ልቦለድ የሚገኘው ዋና ትርጉም የሚመነጨው በልቦለዱ ከሚገኘው ግጭት ነው፡፡ ይህ እንዴት እንደሆነ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማወዳደር አስረዳ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) የበርካታ አጭር ልቦለዶች ጭብጥ የሰዎችን ባህርያት ገላልጦ የሚያሳይ ነው፡፡ ያጠናሃቸው ሁለት ደራስያን ገፀባህርያቶቻቸውን እንዴት እንዳቀረቡዋቸው በማወዳደር ግለጽ፡፡

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

**6.** ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)::

(ሀ) ስነጽሁፍ የሰውን ልጅ ውስብስብና የተለያየ ባህሪና ተፈጥሮ ለመመልከት ያስችላል:: ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር መልስ ስጥ::

ወይም

(ለ) የስነጽሁፍ ስራዎች ህይወትን እንድንገነዘብ የማድረግ ሀይል አላቸው:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አብራራ::

ወይም

(ሐ) ማንኛውንም የስነጽሁፍ ስራ ስናነብ ከምንኖርበት የገሃዱ አለም ወደምናባዊው አለም እንኄዳለን:: ይህንን ሃሳብ ቢያንስ በሶስት ምሳሌዎች አስረዳ::

ወይም

(መ) ስነጽሁፍ የሚነበብና የሚተረጎም አስደሳች ስራ ነው:: በዚህ ሃሳብ የምትስማማበትንም ሆነ የማትስማማበትን ምክንያት በሁለት ስራዎች ምሳሌነት አብራራ::